## *ሁለት ቋንቋ ከአንድ ቋንቋ የተሻለ ነዉ*

### ሁለት ቋንቋን መናገር ጥቅም እንጅ ጉዳት አይደለም

ሁለተኛ ቋንቋን ለመናገር የሚማሩ ልጆች የተለያዩ ጠባያትን ሊያሳዩ ይችሉ ይሆናል። አንዳንዶቹ ዝምታን በመምረጥ ከሌሎች ልጆች ጋር መሳተፍን ያለመፈለግ ጠባይ ሲያሳዩ፤ ሌሎቹ ደግሞ ቋንቋ መማሩን ወዲያዉኑ ሊለምዱት ይችላሉ። እንግሊዝኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ልጆች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታቸዉን ወዲያዉኑ ካላሳዩ የቋንቋ ችግር እንዳለባቸዉ ተደረገዉ በስህተት ሊታዩ ይችላሉ። በአዉስትራሊያ የሚድጉና በአዉስትራሊያ ትምህርት ቤቶች ዉስጥ የሚማሩ ልጆች የሚፈልጉትን ጊዜ ወስደዉ የእንግሊዝኛን ቋንቋ ይማራሉ።

### ሁለት ቋንቋን መናገር የመማር ችግር ሳይሆን የትምህርት ሂደት ነዉ

ብዙ ወላጆች ልጆቻቸዉ መዋለ ሕጻናት (ኪንደርጋርደን) ከመጀመራቸዉ በፊት የእንግሊዝኛን ቋንቋ የማይናገሩ ከሆነ ከሌሎች ልጆች ተነጥለዉ ይታያሉ ወይም እንደሌሎች ልጆች እኩል አይታዩም ብለዉ ይጨነቃሉ። ወላጆችና ልጆች ቋንቋቸዉን እንዳይናገሩ በማበረታታት እንግሊዝኛን ብቻ ተናገሩ የተባለበት አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ። ብዙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንግሊዝኛ የመጀመሪያ ቋንቋቸዉ ላልሆነ ልጆች (Non English Speaking Backgrounds – NESBN) እንግሊዝኛ ቋንቋን የሚያሰተምሩበት የትምህርት ክፍለ ጊዜ እንዳላቸዉ አብዛኛዉን ጊዜ ወላጆችና አስተማሪዎች አያዉቁም። የሚሰጠዉ ፕሮግራም የእንግሊዝኛን ቋንቋ ከማሰተማሩም በላይ ልጆች የመጀመሪያ ቋንቋቸዉን መጠቀማቸዉን እንዲቀጥሉ አብሮ እገዛ በማደረግ ስኬታማ እንደሚሆን አስተማሪዎች ለወላጆች ቢያስረዱ፤ የወላጆችን ጭንቀት ሊቀንሰ ይችላል።

### የመጀመሪያ ቋንቋ ጨርሶ ይረሳል

ልጆች የእንግሊዝኛን ቋንቋ በመማር ላይ እያሉ የመጀመሪያ ቋንቋቸዉን እንዲጠቀሙበት በተደጋጋሚ ካልተበረታቱ ሲያድጉ የመጀመሪያ ቋንቋቸዉን ሊረሱት ይችላሉ ወይም ቋንቋቸዉን ለመናገር ፍላጎቱ ላይኖራቸዉ ይችላል። ልጆችና ቤተሰቦች ሁለት ቋንቋ መናገራቸዉ በአሰተማሪዎች መደገፉ አስፈላጊ ነዉ።

### ቋንቋን መማር ማህበራዊ እንቅስቃሴ ሲሆን በተለያዩ ባህሎች ዉስጥ ሊከናወን ይችላል

ልዩነትን በሚመለከተ የምንወስደዉ እርምጃ ልጆች ላይ በተለይም እንግሊዝኛን ቋንቋ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ሌላ ባህልና ቋንቋ ያላቸዉ (children from Culturally and Linguistically Diverse (CALD) ) ልጆች ላይ ዘላቂነት ያለዉ ተፅእኖ ሊኖሩዉ ይችላል። ቋንቋንና ባህልን በሚመለከት ለልጆችና ለቤተሰቦች የሚሰጠዉ ሃሳብና አመለካከት ቀና ካልሆነ ወይም በትክክል ካልተገለጸ ልጆች ቋንቋቸዉን መማርን ሊንቁና የመጀመሪያ ቋንቋቸዉን ጠብቆ ለማቆየት ወደ ኋላ ሊሉ ይችሉ ይሆናል።

*ልጆች ያላቸዉን ልዩነትና ከተለያየ ቦታ መምጣታቸዉን በቀና በሚመለከት የትምህርት አሰጣጥ ሂደት ላይ ተካፋዮች ከሆኑና ሁለት ቋንቋ መናገራቸዉ በተከታታይ ከተበረታታ በማንነታቸዉ ጽኑ እምነትና ደህንነትን ኖሯቸዉ ያድጋሉ።*

ETHNIC CHILD CARE, FAMILY AND COMMUNITY SERVICES CO-OPERATIVE LTD

Children's Services Central

ይሄ አነስተኛ መፅሄት በ ኢቲኒክ ቻይልድ ኬር ፋሚሊ ኤንድ ኮሚዉኒቱ ሰርቪስስ ኮኦፐረቲቭ ሊሚትድ (Ethnic Child Care Family and Community Services Cooperative Ltd (ECCFCSC)) የባህል ድጋግ ፕሮግራሙ (BSP) አንድ ክፍል በመሆን ነዉ የተዘጋጀዉ። በገንዘብ የሚደገፈዉ በአዉስትራሊያ መንግስት ነዉ። The BSP is run by ECCFCSC for Children's Services Central (CSC). CSC is the Professional Support Coordinator in NSW and is funded by the Australian Government under the Inclusion and Professional Support Program.

Ethnic Child Care Family and Community Services Cooperative Ltd.
Building 3, 142 Addison Rd,
Marrickville, NSW, 2204
ስልክ 02 9569 1288
ፋክስ 02 9550 9829
ኢንተርኔት www.eccfcsc.orrg
ኢሜል coop@eccfcsc.org

ምስጋና

Dr Criss Jones Diaz, Senior Lecturer University of Western Sydney

Belonging, Being and Becoming; The Early Years Learning Framework (EYLF) Government of Australia 2009

Amharic

# ሁለት ቋንቋን መናገርና ቋንቋን መማር

**"ልጆች በመጀመሪያ ቋንቋቸዉ ሲጠቀሙ (ሲናገሩ፤ ሲጽፉና ሲያነቡ) በማንነታቸዉ ጽኑ እምነትና ደህንነትን ይሰማቸዋል።"** *(EYLF 2009)*



ይሄን አነስተኛ መጽሄት www.eccfcsc.org ድህረ ገጽ ላይ ያገኙታል። በሌሎች ቋንቋዎችም ተተርጉሟል።

# ሁለት ቋንቋን ከሚናገሩ ልጆች ጋር ለሚሰሩ ሰዎች የሚሆን ጠቃሚ ምክር

## ሁለት ቋንቋን መናገር ማለት?

አንድ ሰዉ ሁለት ቋንቋዎችን በአጥጋቢ ሁኔታ መናገር ከቻለ ባይ ሊንጉዋል (bilingual) ይባላል። ሁለት ቋንቋዎችን የመናገር ችሎታ ግን እንደ ሁኔታዉ ይለያያል።

## ልጆች በሁለት አይነት መንገድ ሁለት ቋንቋን ሊናገሩ ይችላሉ

**ባንድጊዜ** - ሁሉቱንም ቋንቋዎች በአንድ ጊዜ አንድ ላይ መናገር መቻል

**ተከታታይ** - አንዱን ቋንቋ መናገር ከቻሉ በኃላ ሁለተኛዉን ቋንቋ ለመናገር መማር

የልጆችን የመጀመሪያ ቋንቋ መደገፍና የቋንቋ ችሎታቸዉ እንዲያድግ ማበረታታት በጣም አስፈላጊ ነዉ። ይሄም ሁለተኛ ቋንቋ እንዲማሩ ሊረዳ ይችላል። አዲስ ቋንቋ ለመናገር ጊዜ ሊወሰድ ይችላል በተጨማሪም አንድ ልጅ ቋንቋዉን ሳይናገር ዝም ብሎ የሚቆይበት ጊዜ ሊኖር ይችላል። ይሄ የዝምታ ጊዜ ከልጅ ልጅ ይለያያል።

## ከአንድ በላይ የሆነ ቋንቋን መማርና መጠቀም ጥቅም እንዳለዉ ምንም ጥርጥር የለዉም። ሁለት ቋንቋን የመናገር ጥቅሙ የሚከተሉትን ያካትታል፤

### ምሁራዊ (ኢንተሌክቹዋል)

- የቋንቋን አጠቃቀምና አሰራር መረዳት
- ተጨማሪ ቋንቋዎችን የመማር ችሎታ
- በሌሎች ትምህርቶች ላይ የበለጠ ችሎታን ማሳየት

### ማህበራዊ

- የተለያዩ ቋንቋዎች መኖራቸዉን መረዳት
- ልጆች የመናገር፤ የማንበብና የመፃፍ መንገድ አንድ ብቻ አለመሆኑን ይማራሉ
- ልጆች የተለያየ ማኅበረሰብ በሚገኝበትና ልዩነቶች ተቀባይነት ባገኙበት ስምምነት በሰፈነበት ማኅበረሰብ ዉስጥ ያድጋሉ
- ልጆች እንግሊዝኛ ቋንቋ መናገር ከማይችሉ የቤተሰብ አባላት ጋር እንዲግባቡና ዝምድናቸዉን እንዲቀጥሉ ያስችላቸዋል

### ባህላዊ

- ልጆች በባህላቸዉ፤ በቋንቋቸዉና በማንነታቸዉ ኩራት እንዲሰማቸዉና እንዲተማመኑ ያደርጋል
- የቤተሰብ የባህል ልምድ እንዲቀጥልና ወደሚቀጥለዉ ትዉልድ ለማስተላለፍ ይረዳል

### ኤኮኖሚ

- በስራ፤ በትምህርትና በማኅበራዊ ጉዳዮች ዉስጥ ለመሳተፍ የወደፊት እድሎች

## ሁለት ቋንቋን የሚናገሩ ልጆችን እንዴት ነዉ የምንረዳዉ?

- ስለ ቋንቋ፤ ባህል፤ ማንነትና ትምህርት ምን አመለካከት እንዳልዎት ያስቡበት
- ቀና የሆነና ሁለት ቋንቋዎችን መናገርን የሚደግፍ ፕሮግራም ከቤተሰቦችዎ ጋር ይቀይሱ
- የእያንዳንዱን ልጅ ቋንቋና ባህልን ይወቁ
- ልጆችን በስማቸዉ ለመጥራት ጥረት ያድርጉ (ሰማቸዉ በትክክል መጥራት ካልቻሉ ይጠይቁ)
- ጠቃሚነት ያላቸዉን ቃሎች ዝርዝር ያዉጡና ይማሩ
- ሁለት ቋንቋ ለሚናገሩ ልጆች የተዘጋጁ መረጃዎችን ይሰብስቡና ከፕሮግራምዎ ጋር በማቀናጀት በየቀኑ ይጠቀሙበት
- የልጆቹን ቋንቋዎች በጹሁፍ፡ በቃልና በዲጂታል (በኮምፒዉተር) ያቅርቡ፤ ይጠቀሙ
- የልጆቹን የመጀመሪያ ቋንቋ የሚናገር ሰራተኛ ይቅጠሩ
- ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ ሰራተኞች በቋንቋቸዉ (እርስ በርሳቸዉ፤ ከልጆችና ከቤተሰቦች)ጋር እንዲነጋገሩ ያበረታቱ
- በቀን ዉስጥ የተለያዩ ቋንቋዎችን ይጠቀሙ፤ አነዚህን ቋንቋዎች መጠቀምዎትን ያሳዩ
- ሁለት ቋንቋ የሚናገሩ ልጆች በቋንቋቸዉ እየተነጋገሩ አብረዉ እንዲጫወቱና እንዲማሩ ያበረታቱ
- ለልጆች የመጀመሪያ ቋንቋቸዉን መጠቀም ጥቅም እንዳለዉና ከአንድ በላይ ቋንቋ በማወቅ ሰኬታማ መሆን እንደሚችሉ ለቤተስቦች መረጃ ይስጡ።

